# የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የስነምግባር ረቂቅ ደንብና ምርጫ 2002!

ከብድሆ bidiho@yahoo.com

መቼም አገራችን በዚህ ጊዜ ትልቅ ጉዳይ ለማስተናገድ ደፋ ቀና እያለች ነው። ምን ትልቅ ጉዳይ ተገኘ ብሎ የሚጠይቅ ሰው ያለ አስመስለኝም። ምክንያቱም ጉዳዩ የአንድ ወይም የሁለት ሰው ጉዳይ ስላልደለና ጉዳዩ የመላ አገራችን ህዝብ ጉዳይ ስለሆነ ሁሉም ያውቀዋል የሚል አስተሳሰብ ስላለኝ ነው።

ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በአገራችን ጠቅላላ ምርጫ ይካሄዳል። አገሪቷም ይህንን ድግስ በብቃት ለመወጣት ደፋ ቀና እያለች እንደሆነ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እየሰማን ነው። መስማት ብቻ ሳይሆን  የምርጫ ካርድም ወስደናል ያልወሰድንም እየወሰድን ነን።

አንድ አገር የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ከፈለገች በመጀመርያ ማድረግ ያለባት ነገር ቢኖር ትክክለኛና ታማኝ የሆነ ምርጫ ማካሄድ ነው። ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጥያቄ በተለያዩ ፖለቲከኞችና ምሁራኖች የተለያዩ ትርጉሞችና ማብራርያዎች ተሰጥተዋል። በመጨረሻ ግን ለሁሉም የሚያስማማና የሁሉም ሃሳብ የሚያቅፍ ትርጉም በአብራሃም ሊንከን አንደበት ውስጥ ተሰማ ። አብራሃም ሊንከን ስለ ዴሞክራሲ ሲገልፅ "Democracy is the act of the Government ruling by the People from the People to the People" ብለዋል። የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዴንት የተናገሩት ንግግር ጠቅለል አድርገን ስናየው ዴሞክራሲ ማለት በህዝብ የሚመረጥ፣ የህዝብን ድምፅ ሰምቶ ችግራቸውን የሚፈታ መንግስት መሆኑን ይነግረናል።

ወደ አገራችን ስንመጣ ደግሞ በሕገመንስቱ አንቀፅ  በአገራችን ህዝቦች ብሄር ብሄረሰቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን ይገልፃል። ይህን የስልጣን ባለቤትነታቸው የሚገለፀው ደግሞ ይጠቅመናል የሚሉትን ተወካይ ወይም መሪ የሚሾሙበት ያልወደዱትን ደግሞ የሚሽሩበት ስልጣን ስላላቸው መሆኑን የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። በመሆኑም መጪውን ጠቅላላ ምርጫ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የህዝባችንን ሉዓላዊነት የሚገለፅበት እንዲሆን መላው የአገራቸን ህዝብ ሕገ መንግስቱ የሰጠውን ስልጣን በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል እላለሁ።

ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ጉዳይ ሰሞኑን በአንዳንድ ሕትመቶች ስለ ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች የፃፉትን ፅሁፍ ስላነበብኩ ያለኝን አስተያየት ለመግለፅ ነው። እንደሚታወቀው

የምርጫ ታዛቢዎች በሶስት ይከፈላሉ። እነሱም የህዝብ ታዛቢዎች፣ የአገር ውስጥ ታዛቢዎችና የውጭ ታዛቢዎች በመባል ይታወቃሉ።

የህዝብ ታዛቢዎች የምንላቸው በየቀበሌው በህዝብ ተመርጠው በየምርጫ ጣብያው ያለውን የምርጫ ሂደትና የካርዱ ቆጠራ የሚታዘቡ ብሎም በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በአባልነት የሚሳተፉ ናቸው። በያንዳንዱ የምርጫ ጣብያ አምስት አምስት የህዝብ ታዛቢዎች ይኖራሉ። እነዚህ ታዛቢዎች ኢትዮጵያዊ ዜግነትና ለህገመንግቱ ታማኝ መሆናቸውን እንዳለ ሆኖ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ገለልተኛ የሆኑና በአካባቢያቸው ህዝብም አመኔታ ያተረፉ መሆን እንደሚገባቸው ይታወቃል። የአገር ውስጥ ታዛቢዎች የምንላቸው ደግሞ ከተለያዩ ሲቪክ ማህበራት የተውጣጡና በምርጫ ቦርዱ ምርጫውን ለመታዘብ ፈቃድ የሚሰጣቸው ናቸው።

ከላይ እንደተገለፀው የአገራችን የስልጣን ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሆናቸውን ይታወቃል። በመሆኑም ምርጫውን በዋነኛነት መታዘብ የሚገባቸውና የሉዓላዊነታቸውን ስልጣን በአግባቡ እየተጠቀሙ መሆናቸውና አለመሆናቸው ለማወቅ ህዝቡ በየግሉ የሚታዘበውን እንዳለ ሆኖ ለኔ ይወክሉኛል ያሏቸውን ገለልተኛ የህዝብ ታዛቢዎች በየምርጫ ጣብያው አምስት አምስት ወክለዋል። የአገር ውስጥ ታዛቢዎችም በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አንቀፅ 78/1 መሰረት ከቦርዱ በሚሰጥ ፈቃድ ምርጫውን ለመታዘብ እንደሚችሉ ይደነግጋል። ይሄ የሚያሳየው የአገራችን ምርጫ በመራጭነትም በመታዘብም ሆነ በማንኛውም እንቅስቃሴ በዜጎቿ መተማመንኗ ነው። እንዲህ ሲሆን ነው የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች እኛ የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ነን የምንለው።

ይህ በእንዲህ እያለ የምርጫው ሰላማዊነት፣ ዴሞክራሲያዊነትና ፍትሃዊነት ከኛ ከኢትዮጵያውያን አልፎ መላው ዓለምም እንዲያውቀው ለማድረግ አገሪቱ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዳሉ ሆነው መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን ሊጋብዝ እንደሚችል በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አንቀፅ 78/2 ይገልፃል። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ጉዳይ ካለ ለምንድነው የአገር ውስጥ ታዛቢዎች መታዘብ ይችላሉ ብሎ ዓለም ዓቀፍ ታዛቢዎች ግን መንግስት ሊጋብዝ ይችላል የሚለው ብለን መጠየቁ ተገቢ ይመስለኛል። በእኔ እይታ ይህን የተባለው ምክንያት አገራችን በማንኛውም እንቅስቃሴ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ይሁን በምታደርገው የልማት እንቅስቃሴ መተማመን ያለባት በዜጎቿና በዜጎቿ ብቻ መሆኑን ለማሳየት ይመስለኛል። ይሄ ደግሞ ልንኮራበት የሚገባ ትልቅ እሴታችን ነው ካልኩ ያጋነንኩ አይመስለኝም።

መጪውን ጠቅላላ ምርጫ በሁሉም መለኪያ የተሻለ ለማድረግ መንግስት ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን ወደ አገራችን እንዲገቡ መፍቀዱ የ 2002 ዓ.ም ምርጫ ዓለም አቀፍ ይሁንታ

እንዲያገኝ ይረዳል። ይህ ደግሞ መንግስት ለምርጫው ዴሞክራሲያዊነትና ፍትሃዊነት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ይመስለኛል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የስነምግባር ደንብ የማውጣት ስልጣን የምርጫ ቦርድ መሆኑን ይታወቃል። በመሆኑም ቦርዱ የደንቡን ረቂቅ አዘጋጅቶ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት እያስተቸው እንደሚገኝ ሰምተናል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የግል ሕትመቶች ስለ ረቂቁ ባወጡት ፅሁፍ ላይ የውጭ ታዛቢዎቹ በድምፅ መስጫ፣ መቁጠሪያ ጣብያዎች አካባቢ ካሜራና ቪድዮ፣ ቴፕ ሪከርደርና የስልክ ካሜራ መጠቀም እንደማይችሉና ታዛቢዎቹ በማንኛውም መንገድ በምርጫ ሂደቱ ላይ ጣልቃ የመግባት ሆነ አስተያየት መስጠት እንደማይችሉ ገልፀው ይህ ደግሞ ተገቢነት እንደሌለው የሚያስመስል እንደምታ ያላቸው ፅሁፎችን ፅፈዋል።

እኔም ለመፃፍ ያነሳሳኝ ነጥብ ቢኖር ይሄ ነገር ነው። በየትኛውም አገር ህዝብ ሲመርጥ ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ ቦታ ያለምንም ጣልቃገብነትና ጫና ነፃ ሆኖ ይመርጣል። በአገራችን ያለ እውነታም ይሄ ነው። የውጭ ታዛቢዎቹ ህዝቡ ድምፁን እየሰጠ እያለ የውሬዉ ካሜራ ፊት ለፊቱ መደቀን አለባቸው ማለት የህዝብ ሉዓላዊነት እንደመንጠቅ ሆኖ ነው የሚሰማኝ። መራጩ በሚመርጥበት ቦታ ላይ ፊት ለፊቱ ካሜራ መደቀን ይቅርና በዓለም አቀፍ ሕግ ማንኛውም መራጭ ድምፁን ሲሰጥ ምንም ዓይነት የሚረብሽ ድምፅ መሰማት እንደሌለበት ነው የሚናገረው። በመሆኑም በረቂቁ ያለውን ሃሳብ ትክክልና ዓለም አቀፍ ይዘት የጠበቀ ሆኖ ነው የሚሰማኝ።

በሌላም የውጭ ታዛቢዎቹ ወደ አገራችን ሲመጡ የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ እንጂ በአገራችን የሚካሄደውን ምርጫ ለማስፈፀም እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባናል። በመሆኑም የውጭ ታዛቢዎቹ ያለውን ሂደት በሕጉ መሰረት ተከታትለው፣ ከሕጉ ያፈነገጠ አካሄድ ካለም በቡድን መሪያቸው አማካኝነት ለምርጫ ቦርዱ ማሳወቅ አለባቸው እንጂ የአገራችን የምርጫ ሂደት ማደናቀፍ አይገባቸውም። የደንቡ ረቂቅ የሚለውም ይሄ ነው። በመሆኑም የውጭ ታዛቢዎቹ በምርጫ ሂደቱ ላይ ጣልቃ መግባት የለባቸውም መባሉ ትክክልና ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው አካሄድ ነው።

አንድ ጓደኛየ ስለ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የስነምግባር ደንብ ረቂቁ ስንወያይ የውጭ ታዛቢዎቹ በምርጫ ሂደቱ ላይ ሕገወጥ አካሄድ ከታዘቡ ለምርጫ ቦርድ ማማከር አይገባቸውም አለኝ። እኔም ግራ ተጋባሁና ከመጀመርያውም ፍቃድ የሰጣቸው ሕጋዊ ተቋም እኮ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ነው። ታድያ ለማን ነው መንገር የሚገባቸው? ብዬ ስጠይቀው መንገር የሚገባቸውማ ለዓለም ህዝብ ነው ብሎ መለሰልኝ። እኔም በአነጋገሩ ተገርሜ የውጭ ታዛቢዎቹ ለዓለም ህዝብ መንገር ያለባቸው በምርጫ ሂደቱ ጊዜ አይደለም። ታዛቢዎቹ የታዘቡትን ነገር በሙሉ ይፋ የሚያደርጉት ምርጫውን ተጠናቅቆ ቦርዱ አሸናፊው ይፋ ካደረገ በኋላ ነው።

ካልሆነ የውጭ ታዛቢዎቹ ረጃጅም እጆች ባሏቸው ሚድያዎች ይሄ ትክክል ነው ይሄም አይደለም ብለው የሚያደናብሩን ከሆነ በተለይ በዴሞክራሲ ሂደት ላይ የምንገኝ አገሮች ወደ ህውከትና ብጥብጥ ሊያመሩን ይችላሉ። ምርጫውም የህዝባችን ሉዓላዊነት ያረጋገጠ ሳይሆን በሌሎች (በውጭ) ፍላጎት ላይ የተመሰረት እንዲሆን ያደርገዋል። ብዬ ስመልስለት መጀመርያ የተናገረውን በዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዳላየውና ሃሳቡም ትክክል እንዳልሆነ ተማምነን ተለያየን።

በመጨረሻ መናገር የምፈልገው ነገር ካለ እኛ ኢትዮጵያን በመጀመርያ መተማመን ያለብን በአገራችን ህዝብ ላይ ነው። ሌሎች ለምርጫው እንደ ማጣፈጫ እንጂ ወሳኞች አድርገን ማየት የለብንም። የትኛውም አገር ከሌላ አገር የምታደርገውን ግንኙነት ለአገሯ ከሚያመጣው ጥቅምና ፋይዳ እንጂ የልብ ወዳጅ የሚባል የለምና እኛም በአገራችን ህዝብ ተማምነን የሚመጡት የውጭ ታዛቢዎችም ህጉ በሚፈቅደው መልኩ እንዲንቀሳቀሱ አድርገን ምርጫውን ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ማድረግ እንደምንችል ለመላው ዓለም ማሳየት ይኖርብናል።

ሰላም!